# ስብሀት እና አዳም – የአንድ ሣንቲም ሁለት ገፅታዎች...

በሰላም

Originally published on የሰላም ገጽ

ስብሀት ለአብ እና አዳም ረታ በፅሁፎቻቸው የሚለዩ፣ ተለይተውም ነጥረው የወጡ፣ የራሳቸው ልዩ የአፃፃፍ ዘዬ ያላቸው፣ ከለመድነው እና ካሰለቸን መንገድ ውጭ ሌላ መንገድ እንዳለ ያሳዩን ድንቅ ፀሀፍት ናቸው፡፡ ሁሌም ጊዜ ሲኖረኝ ደግሜ የማነባቸው፣ አንብቤቸውም የማልሰለቻቸው የነዚህን ደራሲያን ምርጥ ሥራዎችን ነው፡፡

ዛሬ ስለ ሁለቱ ደራስያን ታዝቤ የተደመምኩበትን ነገር ላወሳ ወደድሁ፡፡ እንዳንዱ ደራሲ የራሱ የሆነ የአፃፃፍ ቀለም አለው፡፡ ከሌሎች የሚለይበት...የሚገለፅበት...፡፡ የራስ የሆነ የፅሁፍ አሻራ እንደ ማለት ነው፡፡ አንዳንዴ አንዳንድ ደራሲዎች በጣም ከሚያደንቁት ደራሲ የሚዋሱት ዘዬ ይኖራል፡፡ አንዳንዴ ደግሞ አንዱ ከአንዱ ምንም የመቅዳትም ሆነ የመዋስ ሀሳብ ሳይኖረው የሚፅፉበት ዘዴ እና የፅሁፍ አወቃቀራቸው ምስስሎሽ ይታይበታል፡፡ የአዳም ረታን እና የስብሀት ለአብን ፅሁፎች በብዛት ላነበበ እና ትንሽ ላገናዘበ ሰው ሁለቱን ፀሀፍት የምታገናኛቸውን አጠር ብላ የቀጠነችዋን ጠባብ መንገድን አጮልቆ ማየት ይችላል፡፡ በነጥብ ለማስቀመጥ ያህል በሁለቱ ፀሀፍት መሀከል ያለውን የአፃፃፍ ዘይቤ እና የዝንባሌ ምስስሎሽ በሶስት ዋና ዋና ርዕሶች ተቀንብቦ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## ፩. ፋንታሲ – ተረት/ሚትዮሎጂ

አዳም ተረት ይወዳል፡፡ ስብሀትም እንዲሁ፡፡ አዳም ይህን በግልፅ በአንድ ቃለ-ምልልስ ውስጥ የገለፀ ሲሆን ስብሀትም በተፃፈለት ባዮግራፊ ውስጥ ተናግሮታል፡፡ ሁለቱ ደራሲያን ለተረት እና ሚትዮሎች ያላቸው ፍቅር እና ዝንባሌ በሚፅፉት ነገር ላይ በደንብ ይስተዋላል፡፡ አዳም በግራጫ ቃጭሎች (ስለ ሞጆሌዎቹ፣ ስለ እንሽላሊቶቹ፣ ስለ ነጯ ጠጠር...)፣ ከሰማይ የወረደ ፍርፍር (ዋናው ታሪክ)፣ ዱለት፣ ጉሬና ጎሮ፣ የብሩክታዊት ጠጠር እና በመሳሰሉት ድርሰቶቹ ውስጥ ተረት እና ፋንታሲን ቀላቅሎ ግራ አጋብቶናልም...አስደምሞናልም፡፡

ስብሃት ለአብ በበኩሉ በዝነኛው ኢጋፋሪ እንዳሻው በኩል ተረት እና እውነት ቀላቅሎ ሲተርክልን...በአቶ አልአዛር በኩል በፋንታሲ ሲያናውዘን...በኮምቦጥር ያስደመመንን የምንዘነጋው ነገር አይደለም፡፡ ከድርሰቶቹ በተጨማሪ በተለያዩ መፅሄቶች እና ጋዜጦች ላይ ደራሲው ያቀርባቸው የነበረው ተረት መሰል ፋንታሲ ፅሁፎች እና የአፈ-ታሪክ ፅሁፎች ብዙ ነበሩ፡፡

## ፪. ናቹራሊዝም

አንዳንድ በስብሃት ለአብ ላይ የሚነሱ ሂሶች የሚያነጣጥሩት ደራሲው የናቹራሊስም አቀንቃኝ በሆነው በፈረንሳዊው ደራሲ ኤሚሊ ዞላ ተፅዕኖ እንዳለበት በመጥቀስ ነው፡፡ ለዚህ ሂስ ዋና መነሻው የስብሃት አፃፃፍ እንደወረደ የመሆኑ ነገር ነው፡፡...የምንኖርበትን እና የምናደርገውን ነገር እንዳለ በግልፅ መቀመጥ አለበት...መቀባባት ወይም መሸፋፈን የለበትም...ተፈጥሮን/ሕይወትን እንዳለች ከነጉድፏ መግለፅ ነው ያለብን... ነው የሚለው ደራሲው፡፡ ከዚህ አንፃር የደራሲውን ተወዳጅ ሥራዎች የሆኑትን "ሌቱም አይነጋልኝ" እና "ትኩሳት" ማንሳት ይቻላል፡፡

በአዳም ፅሆፎች ውስጥ ናቹራሊዝም በሁለት መልኩ ይታያል

• በአንዳንድ የአዳም ፅሁፎች ውስጥ ባለታሪኮቹ እኛ እንደሆንን ወይም የምናውቀው የእውን ዓለም ሰው እንደሆነ እስኪሰማን ድረስ የሕይወትን እውነታ በጣም የሚያንፀባርቁ ናቸው፡፡ በሌላ አገላፀፅ ገፀ-ባህሪያቱ ለእውኑ አለም በጣም ከመቅረባቸው የተነሳ በሕይወት የምናውቃቸው ሰዎች (እራሳችንን ጨምሮ) ምስሎች ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡

• አዳም በብዙ ፅሁፎቹ ውስጥ ባለታሪኮቹ ከሚያደርጉት ድርጊት ጀርባ ያለውን የተሸፈነ ሀቅ (የዛን ድርጊት ምንጭ) እና የባለታሪኮቹን ጥልቅ ውስጣዊ ስሜት ሊያሳየን ይሞክራል፡፡ ይህ ደግሞ ከናቹራሊዝም አፃፃፍ መለያዎች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ እንደ ናቹራሊስም አቀንቃኞች ከሆነ ሰዎች ባህሪያቸውን የሚያገኙት ካደጉበት ክባቢ፣ ነባራዊ ማህበራዊ ሁኔታ እና ከባህሪ ውርስ ነው፡፡ እና አንድ ሰው የሚገለፀው በነጠላ ለብቻው ሳይሆን ከማህበራዊ ስርአቱ እና ከሚኖርበት ክባቢው አንፃር ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል ለምን መዝገቡ ብቸኛና ግዴለሽ ሆነ? (ግራጫ ቃጭሎች) ለምን ታደሰ ሎሚ ሽታን ከመጀመሪያው ተጠራጠራት? (እቴሜ ሎሚ ሽታ) ለምን ጳውሎስ የምትወደውን እና ልጅ የወለደችለትን ሰላማዊትን ጥሏት ሄደ (ኤልዛቤል)? ለምን ማህሌት የራሷ ምስል የሆነውን ስዕል ሸረካከታ ጣለችው (ማህሌት)? እና ለመሳሰሉት ጥያቄዎች መነሻቸውን ለማጥራት እና የድርጊቶቹን ትክክኛ ምንጭ ምላሽ ለመስጠት መጣሩ የአዳምን ፅሁፍ ከዚህ ወገን እንዲመደብ ያደርገዋል፡፡

የሚገርመው ነገር እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ሁለት የአፃፃፍ ስልቶች (ናቹራሊስም እና ፋንታሲ አፃፃፍ) ፍፁም የተለያዩ መሆናቸው እና በተቃራኒ ፅንፍ የሚቀመጡ መሆናቸው ነው፡፡ ነገር ግን ሁለቱም ደራስያን ከአንዱ ፅንፍ ወደ ሌላኛው በመመላለስ ብዙ ድንቅ ፅሁፎች ፅፈዋል፡፡ በዚህም በአማርኛ ስነፅሁፍ ውስጥ በአንድ ጊዜ በጣም ናቹራሊስት እና በጣም ፋንታሲስት ሆኖ በመፃፍ ስብሃት እና አዳም ከሌሎች ደራሲያን ልዩ ያደርጋቸዋል፡፡

**<u>፫</u>. ደፋር ብዕር**

ስብሀት ሲፅፍ ደፋር ነው፡፡ አዳምም አይፈራም፡፡ እዚህ ጋር ድፍረት/ፍርሃት ከሳንሱር ጥንቃቄ፣ ቃላትን እንደወረደ ከመጠቅም እና በአማርኛ ስነፅሁፍ እንደአይነኬ ተደርጎ ሲታሰብ ከነበረው ስለወሲብ በግልፅ ከመፃፍ አንፃር መሆኑን ልብ ይሏል፡፡ ስብሃት ሌቱም አይነጋልኝ የተሰኘውን ድርሰቱን በፃፈበት ዘመን የነበረው ወግ-አጥባቂነት ሳይበግረው የሕይወትን እውነታ እንደወረደ በመፃፍ ሕይወትን ያለሳንሱር መነፅር ለማሳየት ሞክሯል፡፡

በአዳም ፅሁፎች ውስጥ በቀጥታም ባይሆን ብዙ የፅሁፍ ድፍረት አለ፡፡ በተለይ ወሲብ ነክ ድፍረቶች ጥቂት በማይባሉ ፅሁፎች ውስጥ ይስተዋላል፡፡ ለዚህ ደግሞ "ጭጋግ እና ጠል" ከተሰኘው የአጫጭር ልቦለዶች ስብስብ ውስጥ ከተካተተው አጭር ልቦለድ አንስቶ በቅርቡ በቅንጭብ እስካነበብነው "የስንብት ቀለማት" ድረስ ባሉት የአዳም ሥራዎች ውስጥ ብዙ ማሳያዎች መጥቀስ ይቻላል፡፡ እንደ አንድ ቁንፅል ማሳያ በቅርብ ተቀንጭቦ በወጣው "የስንብት ቀለማት" ልብወለድ ውስጥ በገፅ <u>፩፰</u> እና <u>፩፱</u>የተገለፀውን የወሲብ ትዕይንት ማንሳት ይቻላል፡፡